# አረፍተ ነገሮችን በማዳበር የቃላት አጠቃቀም ችሎታን ማሳደግ

## ኢትዮጲያዊ መመሪያ

(a collaborative method to increase vocabulary..............................)

ኢትዮጲያ ተማሪዎች እንዲስማማ ሆኖ በሮበርት ፐራይስና ኖላዊት ሽመልስ የተዘጋጀ

Robert Seth Price. www.eggplant.org. 2015

## አረፍተ ነገሮችን በማዳበር የቃላት አጠቃቀም ችሎታን ማሣደግ

**መግለጫ (Description)**

አረፍተ ነገሮችን በማዳበር የቃላት አጠቃቀም ችሎታን ማሳደግ ማለት ተማሪዎች የቋንቋ ችሎታከቸውን በንባብና ከእድሜ አቻዎቻቸው በመማማር እንዲያዳብሩ፣ ቃላትን ከነትርጓሜቸው እንዲያውቁና በአረፍተ ነገር ውስጥ ያላቸው የመአገባብ ስርአት እንዲረዱ የሚረዳ ዘዴ ነው፡፡ አረፍተ ነገሮችን ማዳበር የማንበብ ችሎታን ለማሳደግ፣ የቃላትን አቻ ትርጉም ለማወቅ፣ ስዋሰውን ለመረዳት (ግስ፣ ስም፣ ተውላጠ ስም፣ ተውላጠ ግስ ወዘተ) በአጠቃላይ ቋንቋን ለማዳበር ይረዳል፡፡

**ጥንካሬ (Strength)**

አረፍተ ነገሮችን በማዳበር በአንድ ክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎችን ባጠቃላይ ወይም አነስተኛ ቁጥር ያላቸውን ተማሪዎች በመቦደን አሳታፊ በሆነ መልኩ የቃላትና ትርጉም እውቀታቸውን እንዲያሻሽሉ ማድረግ ማለት ነው። ይህንንም ለማድረግ በቀላሉ የሚገኙ ጥቁር ሠሌዳና ጠመኔ መጠቀም ይቻላል። ከመምህሩ በተጨማሪም ተማሪዎች የመማር ማስተማሩን ሂደት እንዲመሩት ማድረግም ይቻላል። ይህም መምህሩ ተማሪዎቹን በጥሩ ሁኔታ ማንበብና ቃላቶችንም ከነትርጉማቸው እንዲያውቁ ለማስተማር እንዲችሉ ይረዳቸዋል ።

መቼ (When)

ይህ የማስተማሪያ መንገድ ከ5-15 ደቂቃ የሚፈጅ ሲሆን ይህንንም በቀን ከአንድ እስከ ሁለት ግዜ ተማሪዎቹ እንዲደጋግሙት ማድረግ እንደምሳሌ የሚቀርቡት አረፍተ ነገሮች የተሻለ ትርጉም የሚሰጡ እንዲሆኑ ይረዳል።

**ቅጥያ (Extension)**


በአንድ አረፍተ ነገር ውስጥ ያሉትን ቃላት በተለያየ ተመሳሳይ ትርጉም ባላቸው ቃላት እንዲተኳቸው በማድረግ፣ በአዲስ መልኩ እንዲጽፏቸው በማድረግ አረፍተ ነገሮችን የማራባት ችሎታቸውን ማዳበር ይቻላል። በተጨማሪም፣ ቃላቶቹ ወቅታዊ ከሆኑት ትምህርቶች ጋር የሚሄዱ አይነት ከሆኑ፣ ግድግዳ ላይ እንዲለጠፉ ማድረግ ይቻላል።

**አቅርቦት (Needs)**

መካከለኛ መጠን ያለው ጥቁር/ነጭ ሠሌዳ ሙሉ አረፍተ ነገር ለመጻፍ የሚያስችል በቂ ስፍራ እንዲሁም ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸውንም ቃላት መጻፊያ ቦታ ይኖረዋል። (Chalkboard Paint??)

**ሂደት** (the process)

1. መምህሩ አረፍተ ነገሩን ሠሌዳው ላይ በዝምታ ይጽፋሉ
2. መምህሩ ቃላቶቹን እየጠቆሙ ጮክ ብለው ያነባሉ
3. መምህሩ ከአረፍተ ነገሩ አንዱን ቃል ምሳሌ ስም ገላጭ ይመርጡና ተማሪዎቹን ተመሳሳይ ትርጉም እንዲሠጡት ይጠይቃሉ
4. መምህሩ ከተማሪዎቹ ጋር በመሆን አዲስ ከነተጨመሩት ቃላት ሙሉ አረፍተ ነገሩን ጮክ ብለው ያነባሉ።
5. መምህሩ ተጨማሪ ቃላትን ተማሪዎቹ እንዲጨምሩ በማድረግ አረፍተ ነገሩን ማስነበብ ይቀጥላሉ
6. ማሳሰቢያ- አንድ ቃል በተጨመረ ቁጥር ሙሉ አረፍተ ነገሩ ጮክ ተብሎ መነበብ አለበት። ይህም ተማሪዎቹ በቀላሉ እንዲረዱት ይረዳል።




**ተማሪዎች በመምህሩ ቦታ (እንደ አስተማሪ)** (Students as a facilitators)


አጠቃላይ የክፍሉን ተማሪዎች ወይንም ከፊሉ የመምህሩን ቦታ ወስደው የአቻ ላቻ መማማሪያ መድረክ ማመቻቸት፣ አጠቃላይ ተማሪዎቹም የሚሳተፉበት ማድረግ

**የመምህሩ ድርሻ** (Teachers Goals of Modeling)

መምህሩ ተማሪዎች የማስተማሩን ድርሻ ወስደው እንዲሠሩ የሚያስችል ስርአት ወይም መመሪያ በማዘጋጀት፣ የተማሪዎችን የመሻሻል ደረጃ በመለካት እንደአስፈላጊነቱ መመሪያውን ማሻሻል

**መመሪያ፣ ቀጣይ ሂደት፣ ቅጥያ** (Procedures, Next Step and Extensions)

**ሂደት** (The Process)




*መምህሩ በዝምታ* *መምህሩ እየመሩ* *ተማሪዎች እየጠቆሙ* *አዲስ ቃል በመጨመር* *በተመሳሳይ ሁኔታ*

*ተማሪዎች እየተመለከቱ* *ተማሪዎች እየተከተሉ* *ሁሉንም አረፍተነገሮች ማለት* *ሌሎቹንም መቀጠል*

**ሂደቱ በተግባር (The process in Action)**

ሂደቱ የክፍሉን ተማሪዎች በጠቅላላ ወይንም በከፊል የሚያካትት ይሆናል። ከዚህ ቀጥሎ የሚኖረው ሂደት ተማሪዎቹን በሙሉ የሚያሳትፍ እንዲሁም የቃላት አጠቃቀም ችሎታቸውን የሚያዳብር ይሆናል። በአረፍተ ነገሩ ውስጥ ያሉት ቃላቶች አዳዲስ ተመሳሳይ ቃላቶች ከተተኩም በኋላ አረፍተ ነገሮቹን ጮክ ብሎ ማንበብ መዘንጋት የለበትም። ይህም የመማር ሂደቱን ከማፋጠኑም በተጨማሪ ተማሪዎቹ እንዲሳተፉበት ይረዳል።

**ስም (Nouns)**

The pig Chased the goat

| | |
|---|---|
| አሳማው ፍየሉን አባረረው | አሳማው ሌላ ምን እንስሳ ማባረር ይችላል |
| ላም | ሌላስ ምን ተመሳሳይ እንስሳ አለ |
| ውሻ | ሌላስ ምን አጥቢ እንስሳ አለ |
| ድመት | |

**ግስ (Verb)**

| | |
|---|---|
| ውሻው ድመቷን አባረራት | አባረራት የሚለውን የሚተካ ሌላ ምን ቃል አለ |
| አሯሯጣት | አሯሯጣት የሚለውን የሚመስል ሌላ ምን ግስ አለ |
| አሳደዳት | |

**የስም ገላጭ (Adjectives)**

ትልቁ አሳማ ፍየሉን አሯሯጠው

| | |
|---|---|
| ወፍራሙ | ለትልቅ ሌላ አቻ ትርጉም ምንድን ነው |
| ግድንግዱ | ለወፍራሙ ተመሳሳይ የስም ገላጭ ምንድን ነው |
| ትንሹ | የትልቅ ተቃራኒ ምንድን ነው |
| ጥቁር | የአሳማው የቆዳ ቀለም ምን አይነት ሊሆን ይችላል |

**ቅጥያ ሃረጎች (Prepositional phrases)**

| | |
|---|---|
| ድመቷ ሜዳው ላይ ትታየኛለች | ድመቷን ሌላስ የት ቦታ ልታዩዋት ትችላላቹ |
| ወጥ ቤት ውስጥ | ድመቷ ምን ውስጥ ልትሆን ትችላለች |
| ጣሪያው ላይ | ሌላስ የት ልትሆን ትችላለች |
| ዛፉ ላይ | ሌላ ቦታስ የት ልታዩዋት ትችላላቹ |

**ተውላጠ ግስ (Adverbs)**

ቅጠሉ መሬተ ላይ በዝግታ ወደቀ

| | |
|---|---|
| በቀስታ | በዝግታን የሚመስል ሌላ ምን ቃል አለ |
| በእርጋታ | በቀስታን የሚመስል ሌላ ምን ተውላጠ ግስ አለ |
| በፍጥነት | በእርጋታ ለሚለው ተቃራኒ የሚሆን ምን ተውላጠ ግስ አለ |
| በቅጽፈት | በፍጥነትን የሚመስል ሌላስ ምን ተውላጠ ግስ አለ |

**ሂደቱን መጨመር (Expanding on the process)**

የቃላት ማዳበሩን ሂደት ለማሳደግና የተማሪዎቹንም የመማር ፍላጎት ለመጨመር ሙሉ አረፍተ ነገሩን መቀያየር የበለጠ ይረዳል። ከዚህ በታች ያለው ምሳሌ የአረፍተ ነገሩን የተለያየ ክፍል በመቀያየር የተመሰረተ ነው።

**የንግግር የተለያየ ክፍሎች ምሳሌ (multiple parts of speech)**

| | |
|---|---|
| ውሻው ድመቷን አባረራት | መምህሩአረፍተ ነገሩን ሠሌዳው ላይ በዝምታ ይጽፋሉ |
| (the dog chased after the cat) | መምህሩ ከተማሪዎቻቸው ጋር ጮክ ብለው ያነባሉ |
| | መምህሩ ለተማሪዎቹን ለግሱ ተመሳሳይ ትርጉም ያብራራሉ |
| | መምህሩ ተማሪዎች አብረው የሚሄዱ ቃላቶች እንዲያስቡ ያደርጋሉ |
| | መምህሩ ተማሪዎች ያሰቡዋቸውን አዳዲስ ቃላት እንዲያካፍሉ ያደርጋሉ |

| | |
|---|---|
| ውሻው ድመቷን አባረራት | መምህሩ ተማሪዎች ካካፈሏቸው ግሶች አንዱን ይጽፋሉ |
| አሯሯጣት | መምህሩ ተማሪዎቹን ሁለቱን አረፍተ ነገሮች ጮክ ብለው እንዲያ ነቧቸው ያደርጋሉ |

| | |
|---|---|
| ውሻው ድመቷን አባረራት | መምህሩ ተማሪዎቹን ተጨማሪ ግስ ይጠይቃሉ |
| አሯሯጣት | መምህሩ ተማሪዎች ካካፈሏቸው ግሶች አንዱን ይጽፋሉ |
| አሳደዳት | መምህሩ ተማሪዎቹን ሁለቱን አረፍተ ነገሮች ጮክ ብለው እንዲያ ነቧቸው ያደርጋሉ |
| | መምህሩ ተጨማሪ ግሶችን እየጥየቁ ይጨምራሉ |

| | |
|---|---|
| ውሻው ድመቷን አባረራት | ከግሡ በተጨማሪ ሌቹንም ቃላት ማራባት |
| ወፏን አሯሯጣት | ከድመት ሌላ ምን ስም እንስሳ መጠቀም ይቻላል |
| አሳደዳት | መምህሩ ተጨማሪ ስሞችን ከተማሪዎች እየጥየቁ ይጨምራሉ |
| ተከተላት | ተማሪዎች ተማሪዎች አረፍተ ነገሮቹን ጮክ ብለው እንዲያነቡ ያደርጋሉ |

| | |
|---|---|
| ውሻው ድመቷን አባረራት | ከድመት ሌላ ምን ስም እንስሳ መጠቀም ይቻላል |
| ወፏን አሯሯጣት | መምህሩ ተጨማሪ ስሞችን ከተማሪዎች እየጥየቁ ይጨምራሉ |
| አይጧን አሳደዳት | መምህሩ ተማሪዎች ሶስቱንም አረፍተ ነገሮቹን ጮክ ብለው እንዲያነቡ ያደርጋሉ |
| ተከተላት | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ውሻው | ድመቷን | አባረራት | ከስምና ግሡ በተጨማሪ ሌቹንም ቃላት ማራባት |
| በጉ | ወፏን | አሯሯጣት | መምህሩ ተጨማሪ ስሞችን ከተማሪዎች እየጥየቁ ይጨምራሉ |
| ላሟ | አይጧን | አሳደዳት | |
| ጦጣዋ | | ተከተላት | |
| አሳማው | | | |

## መዋለ ህጻናት (Early Childhood)

አረፍተ ነገሮችን በማዳበር ህጻናት ቋንቋ፣ ቋንቋ አመሠራረት እና የአረፍተነገር አሠራርን በቀላሉ እንዲማሩ ይረዳቸዋል፡፡ ከዝህም በተጨማሪ፣ አስቀድመው የቃላት አጠቃቀምን በልጅነት እንዲያቅቁ እና የበለጠ ለመማር ፍላጎት እንዲያድርባቸው ይረዳቸዋል። ይህንንም ለማስተማር መምህራን ከመጻሃፍ የተወሰዱ አረፍተ ነገሮችንና የልጆች መዝሙሮችን እንደ ምሳሌ መጠቀም ይችላሉ። አረፍተ ነገር ማራባትን ለመዋለ ህጻናት ልጆች ለማስተማር የልጆች መዝሙሮችን እንደ ምሳሌ እንጠቀም

አስፈላጊ ነገር (needs)

ጥቁር/ነጭ ሠሌዳ፣ ጠመኔ/ማርከር

የሚፈጀው ሠአት (Time)

10-15 ደቂቃ በቀን አንድ ወይም ሁለት ጊዜ

አካሄድ (Process)


መምህሩ የመረጡትን መዝሙር ለልጆቹ ያሳውቃሉ

መምህሩ መዝሙሩን ከተማሪዎቹ ጋር ጮክ ብለው ይላሉ

መምህሩ በሠሌዳው ላይ የተጻፈውን መዝሙር በመጠቀም እየተከተሉ ከተማሪዎቹ ጋር ጮክ ብለው ይላሉ

ተማሪዎቹ መዝሙሮቹን በቃላቸው ይሸመድዳሉ ይይዛሉ

መምህሩ የመዝሙሩን ግጥም ሌሎች ተጨማሪ ትርጉማ  ያላቸው ቃላት ተማሪዎቹን ለማስተማር ይጠቀሙበታል




የተለያዩ የአረፍተ ነገር ክፍሎችን ማዳበር (Multiple Parts of speech)

| | |
|---|---|
| ኧረ ልጆች ልጆች እንጫወት በጣም | መምህሩ በዝምታ አረፍተነገሩን ይፅፋሉ |
| (Oh Little Children lets play lets enjoy) | መምህሩ ተማሪዎቹ በማስነበብ ይማራሉ |
| | መምህሩ ሌሎች ግሶችንም ከተማሪዎች ጋር ይወያያሉ |

(Think –Pair_ share)

| | |
|---|---|
| | መምህሩ ተማሪዎች ተጨማሪ ቃላቶችን እንዲያስታውሱ ይጠይቃሉ |
| ኸረ ልጆች ልጆች እንጫወት በጣም | መምህሩ ተጨማሪ ግስ ከተማሪዎቹ ጥቆማ ይቀበላሉ |
| እንዝናና | መምህሩ ተማሪዎቹ ሁለቱንም አረፍተ ነገሮች እንዲሉ ያደርጋሉ |
| ኸረ ልጆች ልጆች እንጫወት በጣም | መምህሩ ተጨማሪ ግስ ከተማሪዎቹ ጥቆማ ይቀበላሉ |
| እንዝናና | መምህሩ ተጨማሪ ግስ ከተማሪዎቹ ጥቆማ ይጨምራሉ |
| እንደሰት | መምህሩ ተማሪዎቹ ሶስቱንም አረፍተ ነገሮች እንዲሉ ያደርጋሉ |
| ኸረ ልጆች ልጆች እንጫወት በጣም | መምህሩ ተጨማሪ ግስ ከተማሪዎቹ ጥቆማ ይቀበላሉ |
| እንዝናና | መምህሩ ተጨማሪ ግስ ከተማሪዎቹ ጥቆማ ይጨምራሉ |
| እንደሰት | መምህሩ ተማሪዎቹ አራቱንም አረፍተ ነገሮች እንዲሉ ያደርጋሉ |
| እንቦርቅ | ተጨማሪ ግሶችን በመጠየቅ መጨመር |
| እንፈንድቅ | |
| ኸረ ልጆች ልጆች እንጫወት በጣም | ሌላ የአረፍተ ነገር ክፍሎችን መጨመር |
| ህጻናት እንዝናና | ልጆችን የሚተካ ሌላ ስም ምንድን ነው |
| ታዳጊዎች እንደሰት | መምህሩ ተጨማሪ ስሞችን ከተማሪዎቹ ጥቆማ ይቀበላሉ |
| ትንንሾች እንቦርቅ | መምህሩ ተማሪዎቹ ሁለቱንም አረፍተ ነገሮች እንዲሉ ያደርጋሉ |
| እንፈንድቅ | |

ኸረ ልጆች ልጆች እንጫወት በጣም

ህጻናት እንዝናና አብዝተን

ታዳጊዎች እንደሰት

ትንንሾች እንቦርቅ

እንፈንድቅ

| | |
|---|---|
| ኸረ ልጆች ልጆች እንጫወት በጣም | ሌላ ተጨማሪ የአረፍተ ነገሩን ክፍል ማራባት መቀጠል |
| ህጻናት እንዝናና አብዝተን | መምህሩ ተጨማሪ ቃላቶችን ከተማሪዎቹ ጥቆማ ይጨምራሉ |
| ታዳጊዎች እንደሰት በደንብ | |
| ትንንሾች እንቦርቅ | |
| እንፈንድቅ | |

| | |
|---|---|
| ከእንግዲህ ልጅነት ተመልሶ አይመጣም | መምህሩ በዝምታ አረፍተነገሩን ይፅፋሉ |
| | መምህሩ ተማሪዎቹ በማስነበብ ይማራሉ |
| | መምህሩ ልጆች ለሚለው ተጨማሪ ትርጉም ቃል ከተማሪዎች ጋር ይወያያሉ |
| | (Think –Pair_ share) |
| | መምህሩ ተማሪዎች ተጨማሪ ቃላቶችን እንዲያስታውሱ ይጠይቃሉ |

ምሳሌ 2 (Example 2)

| | |
|---|---|
| እኔ ትንሽ ልጅ ነኝ | መምህሩ በዝምታ አረፍተነገሩን ይፅፋሉ |
| (I am a little Child) | መምህሩ ተማሪዎቹ በማስነበብ ይማራሉ |
| | መምህሩ ልጆች ለሚለው ተጨማሪ ትርጉም ቃል ከተማሪዎች ጋር ይወያያሉ |
| | (Think –Pair_ share) |
| | መምህሩ ተማሪዎች ተጨማሪ ቃላቶችን እንዲያስታውሱ ይጠይቃሉ |

| | |
|---|---|
| እኔ ትንሽ ልጅ ነኝ | መምህሩ ተጨማሪ ስም ገላጭ ከተማሪዎቹ ጥቆማ ይቀበላሉ |
| ህፃን | መምህሩ ተማሪዎቹ ሁለቱንም አረፍተ ነገሮች እንዲሉ ያደርጋሉ |

| | |
|---|---|
| እኔ ትንሽ ልጅ ነኝ | መምህሩ ተጨማሪ ስም ገላጭ ከተማሪዎቹ ጥቆማ ይቀበላሉ |
| ህፃን | መምህሩ ተጨማሪ ስም ገላጭ ከተማሪዎቹ ጥቆማ ይጨምራሉ |

| | |
|---|---|
| ታዳጊ | መምህሩ ተማሪዎቹ ሶስቱንም አረፍተ ነገሮች እንዲሉ ያደርጋሉ |

| | |
|---|---|
| እኔ ትንሽ ልጅ ነኝ | መምህሩ ተጨማሪ ስም ገላጭ ከተማሪዎቹ ጥቆማ ይቀበላሉ |
| ህፃን | መምህሩ ተጨማሪ ስም ገላጭ ከተማሪዎቹ ጥቆማ ይጨምራሉ |
| ታዳጊ | መምህሩ ተማሪዎቹ አራቱንም አረፍተ ነገሮች እንዲሉ ያደርጋሉ |
| ሚጢጢ | መምህሩ ተጨማሪ ቃላትን እያስጨመሩ ይቀጥላሉ |

| | |
|---|---|
| እኔ ትንሽ ልጅ ነኝ | ሌላ የአረፍተ ነገር ክፍሎችን መጨመር |
| ሡላም ህፃን | እኔ ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ምን ቃል ይኖራል |
| ታዳጊ | መምህሩ ተጨማሪ ስም ገላጭ ከተማሪዎቹ ጥቆማ ይጨምራሉ |
| ሚጢጢ | መምህሩ ተማሪዎቹ ሁለቱንም አረፍተ ነገሮች እንዲሉ ያደርጋሉ |

| | |
|---|---|
| እኔ ትንሽ ልጅ ነኝ | እኔ እና ሡላም ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ምን ቃል ይኖራል |
| ሡላም ህፃን | መምህሩ ከተማሪዎቹ ጥቆማ ተጨማሪ ስሞችን ይፅፋሉ |
| አፀደ ታዳጊ | መምህሩ ተማሪዎቹ ሶስቱንም አረፍተ ነገሮች እንዲሉ ያደርጋሉ |
| ሚጢጢ | |

**Primary – Upper Primary (Which age group and grade is that??)**

አረፍተ ነገሮችን በማዳበር ታዳጊ ህጻናት ቋንቋ ፣ የቋንቋ አመሠራረት፣ የአረፍተነገር አሠራርን በቀላሉ እንዲማሩና በተለይም ግጥም፣ መዝሙሮችና ታሪኮች ውስጥ የተካተቱ ቃላትን ጠለቅ ያለ ትርጉም እንዲረዱ ይረዳቸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፣ አስቀድመው የቃላት አጠቃቀምን በልጅነት እንዲያውቁ እና የበለጠ ለመማር ፍላጎት እንዲያድርባቸው ይረዳቸዋል። ይህንንም ለማስተማር መምህራን ከመጸሃፍ የተወሰዱ አረፍተ ነገሮችን፣ ግጥሞችንና የልጆች መዝሙሮችን እንደ ምሳሌ መጠቀም ይችላሉ። አረፍተ ነገሮችን በማዳበርን ለመዋለ ህጻናት ልጆች ለማስተማር የልጆች መዝሙሮችን እንደ ምሳሌ እንጠቀም

**አስፈላጊ ነገር (needs)**

ጥቁር/ነጭ ሠሌዳ፣ ጠመኔ/ማርከር

**የሚፈጀው ሠአት (Time)**

10-15 ደቂቃ በቀን አንድ ወይም ሁለት ጊዜ

**አካሄድ (Process)**


*መምህሩ የመረጡትን ግጥሞችና መዝሙር ለልጆቹ ያሳውቃሉ*

*መምህሩ መዝሙሩን ከተማሪዎቹ ጋር ጮክ ብለው ይላሉ*

*መምህሩ በሠሌዳው ላይ የተጻፈውን መዝሙር በመጠቆም እየተከተሉ ከተማሪዎቹ ጋር ጮክ ብለው ይላሉ*

*ተማሪዎቹ መዝሙሮቹን በቃላቸው ይሸመድዳሉ ይይዛሉ*

*መምህሩ የመዝሙሩን ግጥም ሌሎች ተጨማሪ ትርጉማ ያላቸው ቃላት ተማሪዎቹን ለማስተማር ይጠቀሙበታል*




**ቃላት በማዳበር ግጥሞችን ማራባት (Poetry Expansion with Sentence Transformation)**

| *ግጥሙን በተናጠል ወይም አጠቃላይ የክፍሉ ተማሪዎች እንዲያነቡት ማድረግ* | *አረፍተነገርን ማዳበር* | *ተማሪዎቹ ቃላቶቹን በመጠቀም አዳዲስ አረፍተ ነገር ይመሠርታሉ* |
| --- | --- | --- |
| ህልም(Dreams) | | |
| ህልምህን ተንከባክበህ ያዘው | ህልምህን ተንከባክበህ ያዘው | ምኞትህን ጠንቅቀህ እወቀው |
| ኋላ የሞተብህ እንደው | ምኞትህን ጠንቅቀህ ያዘው | ፍላጎትህን አጠንክረህ ውደደው |
| ክንፍ አልባ ወፍ ሆንክ ማለት ነው | ፍላጎትህን አጠንክረህ እወቀው | ቃልህን አጥብቀህ ጠብቀው |
| መብረር እንደማይችለው | ቃልህን አጥብቀህ ውደደው | |
| እንዳልታረሠ እርሻ፣ አረም እንደዋጠው | ተጨንቀህለት ጠብቀው | |
| ህይወትህ ትርጉምም አይኖረው | ጨብጠው | |

**የተለያዩ የአረፍተ ነገር ክፍሎችን ማዳበር (Multiple Parts of speech)**

ህልምህን ተንከባከበህ ያዘው

መምህሩ በዝምታ አረፍተነገሩን ይፅፋሉ

መምህሩ ተማሪዎቹ በማስነበብ ይማራሉ

መምህሩ ልጆች ለሚለው ተጨማሪ ትርጉም ቃል ከተማሪዎች ጋር ይወያያሉ

(Think –Pair_ share)

መምህሩ ተማሪዎች ተጨማሪ ቃላቶችን እንዲያስታውሱ ይጠይቃሉ

ህልምህን ተንከባከበህ ያዘው

ምኞትህን

መምህሩ ተጨማሪ ስሞችን በተማሪዎቹ ጥቆማ ይፅፋሉ

መምህሩ ተማሪዎቹ ሁለቱንም አረፍተ ነገሮች እንዲሉ ያደርጋሉ

ህልምህን ተንከባከበህ ያዘው

ምኞትህን

ፍላጎትህን

ህልምህን ተንከባከበህ ያዘው

ምኞትህን

ፍላጎትህን

ቃልህን

ምሳሌ 2 (Example 2)

ለሠው ልጆች ፍቅር

ለሠው ልጆች ሠላም

ለሠው ልጆች በአለም ዙሪያ ሁሉ

ሠላም ይሁን ምድሩ ሁሉ

ሠላም በአለም ዙሪያ ሁሉ

ለሠው ዘር በሙሉ

**ሁለተኛ ደረጃ (Secondary)**

**Written Sentence Variation with Sentence transformation – what is the difference between these two??**

ተማሪዎች የገብረክርስቶስ ደስታን ኢዮሃ ግጥም ይማራሉ

መምህሩ ግጥሙን ዜማውን ጠብቀው ለተማሪዎች ያነቡላቸዋል

መምህሩ ተማሪዎቹ ግጥሙን በልባቸው (በፀጥታ) እንዲያነቡ ያደርጋሉ

ተማሪዎቹ ጥንድ ጥንድ እየሆኑ ጮክ ብለው ግጥሙን ያነባሉ

መምህሩ ተማሪዎቹ የተረዱትንና ያስተዋሉትን ይጠይቃሉ

አጠቃላይ ተማሪዎቹ ግጥሙን እንዲያነቡ ይደረጋል

መምህሩ የግጥሙን ወሳኝ ክፍሎች በተለያየ ቃላት ያራባሉ

ተማሪዎቹ አዳዲሶቹን ቃላት በመጠቀም ግጥሙን በአዲስ መልክ ይፅፉታል

ተማሪዎቹ (visual map) በመስራት ግጥሙን እንደገና በአዲስ መልክ መፃፍ ይለማመዳሉ

ኢዮሃ (New Year)

አበባ ፈነዳ

ፀሃይ ወጣ ጮራ

ዝናብ ዘንቦ አባራ

ዛፍ አብቦ አፈራ

ክረምት መጣ ሄደ

ዘመን ተወለደ

አዲስ አለም ሆነ

ሌሊት ሲነጋጋ

ጋራው ድንጋይ ከሠል

የተንተረከከው ፍም እሳት ደመናው

ፀሃይ ያነደደው

አለም ሞቆ

ደምቆ

ብርሃን ሲያሸበርቅ

ጤዛው ሲያብረቀርቅ

ህይወት ሲያንሠራራ

ፍጥረት ሲንጠራራ

ዘመን ተለወጠ መስከረም አበራ

እዮሃ አበባዬ

ገብረ ክርስቶስ ደስታ

ከአንድ በላይ የግጥሙን ክፍሎች ማራባት

| | |
|---|---|
| ዛፍ አብቦ አፈራ | መምህሩ ሃረጉን በፀጥታ ሠሌዳው ላይ ይፅፉታል |
| | መምህሩ ከተማሪዎቻቸው ጋር ሆነው ሃረጉን ያነቡታል |
| | መምህሩ ሌሎች ተመሳሳይ ግሶችን ከተማሪዎቻቸው ጋር ይፈልጋሉ |
| | መምህሩ ተማሪዎቹ ግሶቹን እንዲያስቡ፣ እንዲያጣምሩና ለሌሎች እንዲያካፍሉ ያደርጋሉ |

| | |
|---|---|
| ዛፍ አብቦ አፈራ | መምህሩ ሌሎች ተማሪዎቻቸው የጠቆሟቸው ተመሳሳይ ስሞችን ይፅፋሉ |
| አታክልት | መምህሩ ሁለቱን ሃረጎች ተማሪዎች ጮክ ብለው እንዲያነቧቸው ያደርጋሉ |

| | |
|---|---|
| ዛፍ አብቦ አፈራ | መምህሩ ተጨማሪ ጥቆማዎችን ይጠይቃሉ |
| አታክልት | መምህሩ ሌሎች ተማሪዎቻቸው የጠቆሟቸው ተመሳሳይ ስሞችን ይፅፋሉ |
| አበቦች | መምህሩ ሁለቱን ሃረጎች ተማሪዎች ጮክ ብለው እንዲያነቧቸው ያደርጋሉ |

| | |
|---|---|
| ዛፍ አብቦ አፈራ | መምህሩ ተጨማሪ ጥቆማዎችን ይጠይቃሉ |
| አታክልት | መምህሩ ሌሎች ተማሪዎቻቸው የጠቆሟቸው ተመሳሳይ ግሶችን ይፅፋሉ |
| አበባ | መምህሩ ተማሪዎች ጮክ ብለው እንዲያነቧቸው ያደርጋሉ |

ሣር — መምህሩ ተጨማሪ የግስ ጥቆማዎችን ይጠይቃሉ

ዛፍ አበቦ አፈራ — መምህሩ ሌላ የግጥሙን ወሳኝ ክፍሎች በመጨመር ልምምዱን ይቀጥላሉ

አታክልት ፈክቶ — ከአበባ ጋር የሚመሣሠል ሌላ ምን አለ

አበባ ፈንድቶ — መምህሩ የተማሪዎቹን ጥቆማ ያካትታሉ

ሣር — መምህሩ ተማሪዎች ጮክ ብለው እንዲያነቧቸው ያደርጋሉ

ዛፍ አበቦ አፈራ — ከማፍራት ጋር የሚመሣሠል ሌላ ምን አለ

አታክልት ፈክቶ አሸተ — መምህሩ የተማሪዎቹን ጥቆማ ያካትታሉ

አበባ ፈንድቶ ጎመራ — መምህሩ ተማሪዎች ጮክ ብለው እንዲያነቧቸው ያደርጋሉ

ሣር

ዛፍ አበቦ አፈራ — መምህሩ ሌላ የግጥሙን ወሳኝ ክፍሎች በመጨመር ልምምዱን ይቀጥላሉ

አታክልት ፈክቶ አሸተ — መምህሩ የተማሪዎቹን ጥቆማ ያካትታሉ

አበባ ፈንድቶ ጎመራ

ሣር

## Writing with and from sentence transformation

ኢዮሃ (New Year)

አበባ ፈነዳ

ፀሃይ ወጣ ጮራ

ዝናብ ዘንቦ አባራ

ዛፍ አብቦ አፈራ

ክረምት መጣ ሄደ

ዘመን ተወለደ

አዲስ አለም ሆነ

ሌሊት ሲነጋጋ

ጋራው ድንጋይ ከሠል

የተንተረከከው ፍም እሳት ደመናው

ፀሃይ ያነደደው

አለም ሞቆ

ደምቆ

ብርሃን ሲያሽበርቅ

ጤዛው ሲያብረቀርቅ

ህይወት ሲያንሠራራ


ፍጥረት ሲንጠራራ

ዘመን ተለወጠ መስከረም አበራ

እዮሃ አበባዬ

ገብረ ክርስቶስ ደስታ

## Visual Maps with and for Sentence Transformation



Raw raw Raw……….

ምንጭ (Source)

Touching the spirit

የጀርባ ሽፋን (Back Cover)

ማህሙድ አህመድ - ከጉራጌ ማህበረሠብ የተወለደ ኢትዮጲያዊ ድምፃዊ  ነው፡፡ ማህሙድ እውቅናን

ገብረክርስቶስ ደስታ -